

“የባሪያይቱን ውርደት ተመልክቶአልና። እነሆም፥ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል፤ “ ሉቃ ፩ –፵፰



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
የጀርመንና አካባቢው ሀገረ ስብከት
የስዊዘርላንድ ወረዳ ቤተ ክህነት
የጄኔቫ ደብረ መድኃኒት መድኃኔዓለም

## ሃይማኖታዊ ድርጅት


Address : Av d;Aire 3
City : Geneva
Postal code : 1203
Country : Switzerland

Phone : +4179-177-1619, +4178-644-8854, +4178-330-2024

Webpage : https://www.genevamedhanialem.org


# የመድኃኔዓለም ዓመታዊ ንግስ በዓል

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የጄኔቫ ደብረ መድኃኒት መድኃኔዓለም የጥቅምት 2015 የንግስ በዓል ብፁዕ አባታችን አቡነ ዲዮናሲዮስ የጀርመንና አካባቢው ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በተገኙበት እሁድ ጥቅምት 27 ቀን 2015 ዓ.ም በደማቅ ሁኔታ ይከበራል፡፡

.



# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በብሉይ ኪዳን ወይም በአይሁድ እምነት መሠረት ላይ የተመሰረተች ብቸኛዋ ቤተ ክርስቲያን ናት።

የኢትዮጵያውያን ሃይማኖታዊ ሥርዓተ አምልኮ ከንግሥተ ሳባ ዘመን ጀምሮ የነበረ ነው። የሳባ ንግሥት በኢየሩሳሌም ወደሚገኘው የንጉሥ ሰሎሞን ቤተ መንግሥት መጓዝ እንዲሁም በንጉሥ ሰሎሞን እና በንግሥተ ሳባ መካከል ያለውን ግንኙነት ተከትሎ የብሉይ ኪዳን ትምህርት እና እምነት ወደ ኢትዮጵያ ለማስተዋወቅ ተችሏል። የቃል ኪዳኑም ታቦት ወደ ሀገራችን ገብቷል። (፩ ነገ. ፲:፩-፱)

ኢትዮጵያ ክርስትናን የተቀበለችው በአንደኛው ክፍለ ዘመን ከሐዋርያት በቀጥታ ነው። (የሐዋ. ሥራ ፰:፳፯-፴፱ ) በትውፊት እንደተገለጸውም ቅዱስ ማቴዎስ እና ቅዱስ ማርቆስ በኢትዮጵያ ወንጌልን መስበካቸው፣ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም ከልጇ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በስደት በነበረችበት ጊዜ እስከ ኢትዮጵያ ድረስ መምጣቷ ይነገራል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በጌታችን መድኃኒታችን በነቢያትና በሐዋርያት ትምህርት ላይ የተመሰረተ ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ናት።

## ሃይማኖታችን



ሁሉን የፈጠረ አንድ አምላክ በሚሆን በእግዚአብሔር አብ እናምናለን ::ሰማይንና ምድርን የፈጠረ የሚታየውንና የማይታየውን ዓለም ሳይፈጠር ከእርሱ ጋራ በነበረ አንድ የአብ ልጅ በሚሆን፥ በአንድ ጌታ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን።

ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፥ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ እውነተኛ አምላክ፥ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ፥ በባሕርዩ ከአብ ጋር የሚተካከል ሁሉ በእርሱ የሆነ በሰማይም ካለው በምድርም ካለው ያለ እርሱ ምንም ምን የሆነ የለም። ስለ እኛ ስለ ሰዎች እኛን ለማዳን ከሰማይ ወረደ። በመንፈስ ቅዱስ ግብር ከቅድስት ድንግል ማርያም ፈጽሞ ሰው ሆነ። ደግሞም ስለ እኛ ተሰቀለ በጴንጤናዊው በጲላጦስ ዘመን እርሱ መከራን ተቀበለ ሞተ፤ ተቀበረ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ ፤ በቅዱሳን መጻሕፍት እንደተጻፈ በክብር በምስጋና ወደ ሰማይ ዐረገ ። በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ፤ ዳግመኛም በሕያዋንና በሙታን ለመፍረድ በምስጋና ይመጣል ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም።

በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን እርሱም ጌታ ሕይወትን የሚሰጥ ከአብ የሠረጸ፥ ከአብና ከወልድ ጋር በአንድነት እንሰግድለታለን እናመሰግነዋለን እርሱም በነቢያት አድሮ የተናገረ ነው ከሁሉም በላይ በምትሆን ሐዋርያት በሰበሰቡዋት በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንም እናምናለን።

ኀጢአት በሚሰረይባት በአንዲት ጥምቀትም እናምናለንየሙታንንም መነሣት ተስፋ እናደርጋለን የሚመጣውንም ሕይወት ለዘለዓለሙ አሜን።

## አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችን



የደብረ መድህኒት መድኃኔአለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በ2004 ዓ.ም በጥቂት ኢትዮጵያውያን ምእመናን ተመሰረተ፡፡

ብፁዕ አባታችን አቡነ ሕርያቆስ ታቦቱን ባርከው ደብሩን “የጄኔቫ ደብረ መድኃኒት መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን” ብለው ሰይመውታል።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የዕምነቱ ተከታዮች በአቅራቢያ ያሉ ቤተክርስቲያናት እና አዳራሾችን በሰንበት ለጥቂት ሰዓታት በመከራየት የቅዳሴ ሥርዓትን እና የትምህርት አገልግሎትን በማካሔድ ላይ እንገኛለን፡፡

ቤተክርስቲያናችን በፍጥነት እያደገ ያለ ቤተክርስቲያን በመሆኑ ለምዕመኑ ለወጣቶች እና ለህጻናት ተጨማሪ አገልግሎቶችን ለማዳረስና እንዲሁም ለሃገሩ አዲስ የሆኑ ወገኖቻችንን ለማለማመድ ጥረት እናደርጋለን።